የሰ/መ/ቁ. 43160

ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. እንደገና ተሾመ - ቀረቡ፡፡

2. ዳንኤል ባሰ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ ስለተቋረጠብን ልዩ ልዩ በአዋጁ የተመለከቱት ክፍያዎች ይክፈሉን በማለት ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ውሉ የተቋረጠው ዘመኑ በማብቃቱ ነው በማለት ሲከራከር፣ ፍ/ቤት ደግሞ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ነው የሚለውን የተጠሪ ክርክር በመቀጠል የአመልካቾች የውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት ለሚሠሩበት ጊዜ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በውሣኔው ባለመስማማት ይግባኝ ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም ውሉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የተገባ ስለመሆኑ አሠሪው /ተጠሪ/ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ደምድሚል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የሥራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች በሙሉ አመልካቾች ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመቀጠልም የሰበር ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካቾች ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ አቤቱታው ላይ ያለውን መልስ እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ እድል የተሰጠው ቢሆንም፣ የሰጠው መልስ የለም፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተመለከተው ተጠሪ በከፍተኛ ትምህርት መስጠት የተሰማራ ሲሆን፣ አመልካቾችን ቀጥሮ ሲያሠራ የነበረው በመምህርነት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የመማር ማስተማር ሥራ ቀጣይነት ያለው ማለትም የማያቋርጥ ባሕርይ ያለው ሥራ ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ውላችን ያለአግባብ ተቋርጦብናል በማለት ክስ በመሠረቱበት ጊዜ ተጠሪ ሥራውን ሲቀጥል እንደነበረም አላከራከረም፡፡ አመልካቾችን የቀጠርኩት ለተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ሲከራከር የቆየው ሥራው የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ሳይሆን፣ ውሉ የተፈረመው ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ነው በማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ ያቀረበው ክርክር ግን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በፍሬ ነገር ረገድ ሊያስረዳ አልቻለም፡፡ አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችለው በአንቀጽ 10 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት የተደረገ ከሆነ ስለመሆኑ በአንቀጽ 9 ተደንግጎአል፡፡ በመሆኑም ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ተፈርሞአል የሚለው የተጠሪ ክርክር

የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ስናየው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65098 ኅዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13964 ሚያዝያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ